## አይ.ዲ.ደብሊው.ኤፍን ማን ሊቀላቀል ይችላል?

መቀላቀል የሚችሉት የሰራተኛ ማህበራት ወይም ሌላ አይነት አወቃቀር ያላቸው አባላትን መሰረት ያደረጉ ዴሞክራሲያዊ ደንቦች ወይም ልማዶችን የሚተገብሩ በአገርም ሆነ በውጭ አገራት የሚገኙ በቤት ውስጥ ሰራተኞች የሚመሩ ድርጅቶች ናቸው።

እንዲሁም አይ.ዲ.ደብሊው.ኤፍ የአለማቀፉ የፌዴሬሽኖች ህብረት ለምግብና ለሰራተኞች ጥምረት ልዩ የስብስቡ አባልና አለማቀፉ የምግብ፣የግብርና፣ የሆቴል ፣ የምግብ አቅርቦት፣ የትንባሆ እና የሰራተኞች ጥምረት (የ አይ.ዩ.ኤፍ ) እና የሴቶች ህጋዊ ያልሆኑ የስራ ቅጥርና ማደራጃ (የደብልዩ.አይ.ኢ.ጂ.አ) አባልም ነው።

## ለበለጠ መረጃ ከዚህ በታች ባሉት ልታገኙን ትችላላችሁ


ድህረገጽ፡-www.idwfed.org

ኢሜይል፡-info@idwfed.org

ፌስቡክ፡-International Domestic Workers Federation

ትዊተር፡-IDWFED

ጸሐፊዎች፡-c/o CTU Training Center, 18 Shek Lei Street, Kwai Chung, N.T., Hong Kong

ኤልሳቤጥ ታንግ፡- General Secretary, elizabeth.tang@idwfed.org

ቪኪ ካንዮካ፡-Regional Coordinator-Africa, vicky.kanyoka@idwfed.org

ፊሽ አይፒ፡-Regional Coordinator - Asia Pacific, fish.ip@idwfed.org

ካሪን ፓፔ፡-Regional Coordinator -Europe, karin.pape@wiego.org

አድሪያን ጋብሪኤል ፓዝ፡-Regional Coordinator- Latin America, adriana.paz@idwfed.org

ማያ አቢ ሳምራ፡-Regional Coordinator - Middle East and North Africa, may.abisamra@idwfed.org


## ዓለም አቀፉ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ፌዴሬሽን (አይ.ዲ.ደብሊው.ኤፍ) ምንድን ነው? ምንስ ይሰራል አይ.ዲ.ደብሊው.ኤፍ በዝርዝር

# ዓለም አቀፉ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ፌዴሬሽን (አይ.ዲ.ደብሊው.ኤፍ)

ዓለም አቀፉ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ፌዴሬሽን (አይ.ዲ.ደብሊው.ኤፍ) አባላትን መሰረት ያደረገ አለማቀፍ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ድርጅት ነው። ለብዙ ዓመታትም መደበኛ ባልሆኑ ሰራተኞች ውስጥ የተመሰረተ የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የሰራተኛ ማህበር ፌደሬሽን ነው። እንዲሁም በሴት ለመመራትም የመጀመርያው ድርጅት ነው።

ዓላማውም በአለም ዙርያ የቤት ውስጥ ሰራተኞች መብትን ማሻሻልና ማስጠበቅ የሚችል እንዲሁም ጠንካራ ፣ ዴሞክራሲያዊ እና ህብረት ያለው የቤት ውስጥ ሰራተኞች ድርጅት መገንባትና ነው።

የቤት ውስጥ ስራ ራሱን የቻለ ስራ እንደሆነ እናምናለን። ልክ እንደማንኛውም አይነት ሌላ ስራ ሰራተኞች የቤት ሰራተኞችም መብታቸውን ማጣጣም አለባቸው።

አይ.ዲ.ደብሊው.ኤፍ ከአለም ዓቀፉ የሰራተኞች ኔትዎርክ ተነጥሎ ለብቻው በመውጣት እ.አ.አ ከጥቅምት 26-28 / 2013 በሞንቴቪዴዮ ኡራጋይ በተደረገው የኮንግረሱ ምስረታ ላይ አለም አቀፉ ፌዴሬሽን ሆኖ ተቋቋመ።

እስከ 2018 ድረስ በ55 አገሮች ውስጥ ከተመሰረቱ ድርጅቶች ጋር ትስስር ያደረግን ሲሆን ከ600,000 በላይ የቤት ውስጥ ሰራትኞችን መወከልም ችለናል። ትስስር ካደረግናቸው ድርጅቶች መካከል አብዛኞቹ የሰራተኛ ማህበራት ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ የተለያዩ ስብስቦችና የቤት ውስጥ ሰራተኞች የሕብረት ስራ ማህበራት ናቸው።

# አስተዳደር

የአይ.ዲ.ደብሊው.ኤፍ ምክር ቤት አባላት ከፍተኛው የአስተዳደር አካል በየ 5 አመቱ ( የመስራች ምክርቤቱ ስብሰባ በጥቅምት 2013 በኡራጋይ ተይዞ የነበረ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በኬፕታውን ደቡብ አፍሪካ ተሰብስቦ ነበር ) ምክር ቤቱ ለህገ መንግስቱ ክለሳ እና መሻሻል ቅድምያ በመስጠት የስራ አመራሩን ይመርጣል።





የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ቀጣይነት ያለውን አስተዳደርን በመፍጠር በማዕከላዊነት የአይ.ዲ.ደብሊው.ኤፍን አላማ እና ራዕይ በመከተል በአይ.ዲ.ደብሊው.ኤፍ መመርያዎች መሰረት ሰራተኞችን የመደገፍና የመቆጣጠር አስተዳደራዊ ሐላፊነት አለበት።የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከፕሬዚዳንት፣ ከምክትል ፕሬዚዳንት እና ከዋና ጸሐፊ( ጡረተኛ ከፍተኛ የቀድሞ አመራሮች) እና ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የተውጣጣ ነው። በልዩ ሁኔታ ከሚመረጠው ዋና ጸሐፊ በስተቀር ሁሉም ተወካዮች እያንዳንዳቸው ከታች ከተዘረዘሩት አገሮች የሚመረጡ ናቸው፡-ከአፍሪካ፣ ከእስያ/ከፓስፊክ፣ ከደቡብ አሜሪካ፣ ከካሪቢያን፣ከአውሮፓ እና ከሰሜን አሜሪካ። እሷ በማትኖርበት ወቅት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተግባሩን እንዲወጣ ተለዋጭ ተወካዮች ከእያንዳንዱ ክልሎች የሚመረጡ ይሆናል።

የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በአመት ከአራት ላላነሰ ግዜ ይሰበሰባል። እንዲሁም በአካል ቢያንስ አንድ ግዜ ሲሰበሰብ ከሌሎቹ ጋር ደግሞ በቴሌ ኮንፈረንስ (በአካል ተገናኝቶ መወያየት በማይቻልበት ወቅት)ይሰበሰባል። የክክል አስተባባሪዎች ደግሞ ከራሳቸው የስራ አስፈጻሚ ተወካይ ጋር በየአጫጭር ግዜያት ይገናኛሉ። እንዲሁም በሒደት ላይ ያሉ የስራ እንቅስቃሴዎች እና አመራሩ በዋና ጸሐፊው ይመራሉ።





## ሊቀመንበር

**ሚርትል ዊትቡይ**

ከደቡብ አፍሪካ የቤት ውስጥ የሰራተኞች ትብብርና ህብረት።
ከደቡብ አፍሪካ

በኮንግረስ ምስረታው ላይ የአይ.ዲ.ደብሊው.ኤፍ ሊቀመንበር ሚርትል ዊትቡይ ሲናገሩ

ዛሬ የደረስንበት ቦታ ለመድረስ ብዙ ስራ ተሰርቷል። ለዚህም የድርሻቸውን ለተወጡት ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። አሁንም ለሌሎች መጠቀምያ የሆኑ ብዙዎች አሉ አዲሱም ፌዴሬሽን ወደፊት ከባድ ስራ ይጠብቀዋል። ነገር ግን በትክክለኛው አመራር አለምን እንደ አውሎ ነፋስ እናዳርሰዋለን። ከዚህ በኋላ ባርያነታችን ያበቃል። ልክ እንደ ሌሎቹ መብት እንዳላቸው ሰራተኞች እኛም ሰራተኞች ነን። ሊሆን አይችልም የተባለውም ህልም እውነት ሆኗል። ይሄ ለእናንተ እና ስለ እናንተ ነው። ዛሬ ድምጻችሁ እንዲሰማ አድርጉ ።”

ሊቀመንበር፡-
ሚርትል ዊትቡይ ከደቡብ አፍሪካ የቤት ውስጥ የሰራተኞች ትብብርና ህብረት። ከደቡብ አፍሪካ

ምክትል ሊቀመንበር፡-
ካርመን ብሪትዝ፣ ዩ.ፒ.ኤ.ሲ.ፒ , ከአርጀንቲና

ዋና ጸሐፊ፡-
ኤልሳቤጥ ታንግ, አይ.ዲ.ደብሊው.ዲ.ኤፍ ጸሐፊ, ከሆንግ ኮንግ

**የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት**

ኖቨሊታ ቫልዴዝ ፓሊሶክ, የተባበሩት ,ከፊሊፒን
ሺርሊ ፕሪስ , ጄ.ኤች.ደብሊው.ዩ , ከጃማይካ
ግሬስ ፓፓ, ሴ.ኤስ.ሲ አ&ኤስ , ከቤልጂየም
አንደሪያ ደል ካርመን ሞራሌዝ ፔሬዝ , ኤፍ.ኢ.ቲ.አር.ኤ.ዲ.ኦ.ኤም.ኦ .ቪ , ከኒካራጓ
ጊልዳ ቪክቶሪያ ብላንኮ ፍራንዟ , ኤን.ዲ.ደብሊው.ኤ , ከዩ.ኤስ.ኤ

**አማራጭ የስራ አስፈጻሚ የኮሚቴ አባላት**

አስማው ባህ , ኤስ.ዋይ.ኤን.ኢ.ኤም - ጊኒ , ከጊኒ
ዊንዲ ፓውል ጋላርዛ ኩዊኖኔዝ , ኤፍ.አይ.ኤል.ሲ.ኤ.ኤም.ኤስ ሲ.ጂ.አይ.ኤል , ከጣልያን
ጊያኑ ማያ ክሻስትሪ , ኤህ.ዩ.ኤን , ከኔፓል
ኖርማ ኔልሰን , ኤቲ.ኤል.ዩ ,ከአንቲጓ እና ከባርቡዳ
ዱግ ሞሬ , ዩ.ዲ.ደብሊው.ኤ , ከዩ.ኤስ.ኤ

# ከምን ተነሳን?

“የቤት ውስጥ ሰራተኛ ማን ነው? ”
ማንኛውም በቤት ውስጥ የስራ ስምሪት ዘርፍ የሚሰራ ሰው ማለት ነው።

## ዓለም አቀፍ የቤት ውስጥ ሠራተኞች ኔትወርክ (IDWF) እና C189፡፡

ያኔ ገና 2006 ውስጥ ነበር ለመጀመርያ ግዜ ከአለም ዙርያ የቤት ውስጥ ሰራተኞች፣ የተለያዩ ድርጅቶች እና ደጋፊዎቻቸው በአንድነት ለዓለም አቀፍ ስብሰባ የመጡት፤ በስብሰባውም አለማቀፍ የቤት ውስጥ ሰራተኞች መረብን (አይ.ዲ.ደብሊው.ኤን) በበመስረት የአይ.ኤል.ኦ ን የቤት ውስጥ ሰራተኞች እንደሰራተኛ የመታሰብ መብት ስምምነትን ለማስጠበቅ በጋራ ለመታገል አዲስ መረብ ለመዘርጋት ወሰንን። እነዚህን መብቶች በቀደሙት ግዜያት የተከለከሉ ቢሆንም።
በጥረታችንም ከአይ.ዩ.ኤፍ፣ ከደብሊው.አይ.ጂ.ኦ ፣ ከአለማቀፍ የሰራተኞች ህብረት ኮንፌዴሬሽንም (አይ.ቲ.ዩ.ሲ) ልክ እንዲሁ እንደ ሌሎቹ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከፍተኛ እገዛን አግኝተናል። በሰኔ 2011 እ.አ.አ በተደረገው ከአር 201 ጋር ተያይዞ አይ.ኤል.ኦ ባቀረበው ሲ 189 ተመጣጣኝ ስራ ለቤት ውስጥ ሰራተኞች ስምምነት ላይ በስብሰባው በተገኙ የዓለም አቀፍ መንግስታት ተወካዮች ፣ አሰሪዎች እና በዓለም አቀፉ የሰራተኞች ድርጅት (አይ.ኤል.ኦ ) ዓለም አቀፍ የሰራተኞች ስብሰባ ላይ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ድል አግኝተናል።

### ለመደራጀት የነበሩ ከፍተኛ ችግሮች

- ድብቅ እና ግልጽ ያልሆኑ በቤት ውስጥ ያሉ ተፈጥሯዊ የስራ ባህሪያት
- አሰሪዎችን ጾታዊ ትንኮሳ ፣ ጥቃትና ከስራ መባረር ይደርስብኛል ብሎ መፍራት
- መኖርያ ቤትን፣ ምግብን እና የመኖርያ ፈቃድን በተመለከተ በአሰሪዎች ላይ ጥገኛ መሆን
- በሰራተኛው ህግ ከለላ ያለማግኘት
- ረጅም የስራ ሰአት፣ እረፍት ወይም የእረፍት ሰአት ያለመኖር እና በበዓላት ቀናት እረፍት ያለመኖር
- የህግ አስፈጻሚ አካላትን መፍራት

### ዋና ዋና የስራ ቦታዎች

አይ.ዲ.ደብልዩ.ኤፍ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ጠንካራ ፣ ዴሞክራሲያዊና ዘላቂነት ያለው የሰራተኞች ድርጅት እንዲያቋቁሙ እንዲሁም ይህንን ድርጅት በአለም ዙርያ በማንቀሳቀስ ተጽእኖ ፈጣሪ በማድረግ የቤት ውስጥ ሰራተኞችን መብትን የሚያስጠብቅ እና ተደማጭነት ያለው ፌዴሬሽን ለመመስረት ይሰራል። አይ.ዲ.ደብሊው.ኤፍ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በመከወን ለውጤታቸው ይተጋል፡-

- በየአካባቢው የሚገኙ የቤት ውስጥ ሰራተኞችን በመመልመል አባላትን መሰረት ያደረጉ ጠንካራ ድርጅቶችን እንዲያቋቁሙና ሴቶችንም በማደራጀት የአመራርነት ድርሻቸው እንዲጠነክር ድጋፍ ማድረግ።
- የአይ.ኤል.ኦ ስምምነት 189 እና ሌሎችም የቤት ውስጥ ሰራተኞች እንቅስቃሴዎች እንዲጸድቁ እና ተግባራዊ እንዲሆኑ ዘመቻዎችን ማዘጋጀት ወይም ለዘመቻዎች ድጋፍ ማድረግ።
- የቤት ውስጥ ሰራተኞችን ግንዛቤ ለማጠንከር በድርጅቶቻቸው ላሉ አባላቶቻቸው እና ደጋፊዎቻቸው የተለያዩ የትምህርትና የተግባር ስልጠናዎችን በመስጠት እንዲሁም እርስ በእርሳቸው የተለያዩ ገምቢ ልምዶቻቸውን እንዲለዋወጡ ሁኔታዎችን ማስተካከል ።
- በተለያዩ በአገር ውስጥ ባሉ አካባቢዎች፣ክልሎች እና በአለማቀፍ ፎረሞች ላይ የቤት ውስጥ ሰራተኞችን በመወከል መገኘት።
- ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር በቋሚነት በመገናኘት በአይ.ዲ.ደብሊው.ኤፍ የወደፊት ህይወት ውስጥ የራሳቸውን አስተዋጾ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።
- በተለያዩ የሰራተኛ ማህበራትና ህብረቶች እንዲሁም ሌሎች አጋር ድርጅቶች አማካኝነት ለቤት ውስጥ ሰራተኞችና ድርጅቶቻቸው ጥቅም አስተማማኝ ግንኙነቶችን በመገንባት፣በማስተዋወቅና ትስስሮችን በመፍጠር የቤት ውስጥ ሰራተኞችን ግብአት ማሳደግ።